በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ.ቁ.209733

ህዳር 27/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡ 1. ዳዊት መንገሻ } የቀረበ የለም

2. አበራሽ በዳኔ

ተጠሪ፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ- የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 675(1) ድንጋጌን ጠቅሶ በአሁን አመልካቾች ላይ በባሌ ዞን ጋሰራ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት አመልካቾች የማይገባቸውን ብልፅግና ለራሳቸው ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስበው በወንጀል ተጠርጥሮ በክፍሉ ፖሊስ በቁጥጥር ስር ውሎ የነበረው በአጠቃላይ 656 ቁምጣ የዳንጎቴ ሲሚንቶ በወቅቱ በወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት ንብረቱን ለማስቀመጥ የሚያስችል ቦታ ባለመኖሩ በአሁን አመልካቾች መጋዘን እንዲራገፍ ተጠይቀው ፈቃደኛ በመሆናቸው ንብረቱ በህገ ሲፈለግ ለማቅረብ ተስማምተው 1ኛ አመልካች 310 ቁምጣ፤ 2ኛ አመልካች ደግሞ 346 ቁምጣ ሲሚንቶ ከወረዳው ገቢዎች ጽ/ቤት ሰራተኛ ፈርመው በአደራ ከተቀበሉ በኋላ ሲሚንቶውን እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ለማቅረብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

አንደኛ አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ በክሱ ውስጥ የተጠቀሰው ንብረት በህጋዊ መንገድ የገዛሁት የራሴ ንብረት ነው፤ ሲሚንቶውን ሳራግፍ ህገ ወጥ ነው የሚል ጥያቄ ተነስቶ እስኪጣራ ድረስ እንዳራግፍ ተፈቅዶ በዚሁ መሰረት ያራገፍኩት እንጂ በአደራ የተቀበልኩት አይደለም፤ ንብረቱም

በኤግዚቢትነት ያልተመዘገበ በመሆኑ ልከሰስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሁለተኛ አመልካች በበኩላቸው ንብረቱ የአንደኛ አመልካች ነው፤ በመጋዘኔ እንዳስቀምጥላቸው ጠይቀዉኝ ያስቀምጥኩት እንጂ በክሱ ውስጥ በተገለፀው አግባብ በአደራ የተቀበልኩት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ አመልካቾች ለወንጀል ክሱ ምክንያት የሆነውን ንብረት በክሱ ዝርዝር በተገለፀው አግባብ በአደራ ተቀብለው እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ያላቀረቡ ስለመሆኑ በዐቃቤ ህግ የሰው እና አመልካቾች ንብረቱን በአደራ ስለመቀበላቸው በፈረሙት የአደራ ሰነድ የተረጋገጠ መሆኑን፤ በአንፃሩ አመልካቾች ንብረቱን በአደራ የተቀበልነው ሳይሆን የአንደኛ አመልካች ነው በሚል የተከራከሩ ቢሆንም አቅርበው ባሰሟቸው የሰው ምስክሮች የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃን አላስተባበሉም በሚል ክስ በቀረበበት አንቀፅ ስር ጥፋተኛ ብሎ እያንዳንዳቸውን በ6(ስድስት) ወር ቀላል እስራ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

ይህንኑ ጉዳይ በይግባኝ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ አመልካቾች ለወንጀል ክሱ ምክንያት የሆነውን ሲሚንቶ የተረከቡት በውል ስምምነት በመሆኑ የውል ግዴታቸውን ካልፈፀሙ በፍትሓ ብሄር ከሚጠየቁ በቀር በወንጀል የሚያስጠይቃቸው ነገር የለም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/65054 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በዋቢነት ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ውድቅ በማድረግ አመልካቾን ከቀረበባቸው ክስ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ አመልካቾች በአደራ ለማስቀመጥ የተረከቡትን ንብረት ሲጠየቁ ማቅረብ እንዳልቻሉ ተረጋግጦ እያለ እና ይህንን ሊያስተባብል የሚችል መከላከያ ማስረጃ ባልቀረበበት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾችን በነፃ ማሰናበቱ አግባብ አለመሆኑን በመተቸት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ውድቅ አድርጎ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን አፅንቷል፡፡ ይኸው ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ሰኔ 22/2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች በአደራ የተሰጣቸውን 656 ቁምጣ ሲሚንቶ እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ባለማቅረባቸው የወንጀል ህግ አንቀፅ 675(1) በመተላለፍ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅመዋል በሚል የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠበት አግባብነት በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በሰበር አጣሪ ችሎት በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙ በፅሁፍ ባቀረቡት መከራከሪያም ከሞላ ጎደል በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን መከራከሪያዎች በመድገም ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ይህንን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ አመልካቾች የተከሰሱት በእምነት ማጉደል ወንጀል ነው፡፡ የእምነት ማጉደል ወንጀል ምን ማለት እንደሆነ እና የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች በወንጀል ህጉ አንቀፅ 675 ስር ተመልክቷል፡፡ በዚሁ አግባብ አንድ ሰው የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ በወንጀል የሚቀጣው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግናን ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውን እና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ፣ ወይም ይህንን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

የፈፀመ እንደሆነ እና ይህንኑ በእምነት ወይም በአደራ የተቀበለውን ንብረት ወይም ጥሬ ገንዘብ እንዲመልስ ወይም እንዲከፍል ሲጠየቅ ንብረቱ ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው ለመሆኑ ማስረዳት ያልቻለ ስለመሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ከዚሁ ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 3 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከእነዚህ የእምነት ማጉደል ወንጀል ማቋቋሚያ መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ውስጥ አንዱ በአደራ የተቀበሉትን ንብረት እንዲመልስ ሲጠየቅ አለመመለስ እንደሆነ በዚሁ ድንጋጌ ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካቾች የእምነት ማጉደት ወንጀል ፈፅመዋል የተባሉት በህገ ወጥነት ተጠርጥሮ በቁጥጥር ስር የዋለውን ንብረት በአደራ እንዲያስቀምጡ የተሰጣቸውን ንብረት ሲጠየቁ አላቀረቡም በሚል ነው፡፡ አመልካቾች ንብረቱን በተመለከተ የባለቤትነት መከራከሪያ ያቀረቡ ቢሆንም ማስረጃን የመስማት እና የመመርመር ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ለወንጀል ክሱ መሰረት የሆነው ንብረት አመልካቾች በአደራ ለማስቀመጥ ፈርመው ከህግ አካል የተቀበሉት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን ከስር ፍርድ ቤቶች የመዝገብ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካቾችን ከወንጀል ክሱ በነፃ ሲያሰናብት በምክንያትነት የጠቀሰው ጉዳዩ ወንጀል ሳይሆን የውል ግዴታን አለመፈፀምን የሚመለከት ፍትሓ ብሄራዊ ኃላፊነት ነው በሚል እንጂ ንብረቱ የአመልካቾች ስለመሆኑ አስረድተዋል በሚል አይደለም፡፡ በእርግጥ አመልካቾች ንብረቱን በአደራ ፈርመው መቀበላቸው በግራ ቀኙ መካከል ያለው ግኑኝነት የውል የሚያስመስለው ነው፡፡ ሆኖም የውሉ ጉዳይ በአደራ የተቀበሉትን ንብረት በአደራ ሰጪው ሲጠየቁ ለመመለስ እንጂ ለሌላ ዓላማ ባለመሆኑ በዚህ መልኩ አምነዉበት የተቀበሉትን ንብረት እንዲመልሱ ሲጠየቁ አለመመለስ ተራ የውል ግኑኝነትን የሚመለከት ሳይሆን የእምነት ማጉደል ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ያዩበት እና የደረሱበት ድምዳሜ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር እና ክስ የቀረበበትን የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር ሊነቀፍ የሚችልበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ/374852 ላይ ግንቦት 10/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2))) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም